# ጢስ እሳት ዉሃ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር
# /ጢእዉስ/

## ብሄራዊ ግልጽ ጨረታ ሰነድ

**የጨረታ ቁጥር፤ ጢእ/04/2026**

**ጨረታዉ የወጣበት ቀን፤ መጋቢት 22, 2018**

**አዲስ ዘመን ጋዜጣ**

## የተለያዩ ጎማዎች እና የማሽነሪ መለዋወጫዎች ግዥ

**ባህር ዳር፤ ኢትዮጵያ**

Tel:+251582204826 E-mail: contact@tisisat.com Website:www.tisisat.com
F ax: +251582204830 P.O.Box.: 840 Face Book:Tis Isat Water Works PLC

Scanned with CamScanner

Tis Isat water works plc
ጢስ እሳት ውሃ ስራዎች ኃ/የተ/የግል/ማ

# የጨረታ ማስታወቂያ

ኩባንያችን ጢስ እሳት ዉሃ ስራዎች የተለያዩ ጎማዎችን እና የማሽነሪ መለዋወጫዎችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ግዥ መፈፀም ይፈልጋል፡፡

| ሎት | የእቃዉ አይነት | የጨረታ ማስከበሪያ | የማቅረቢያ ቀን |
|---|---|---|---|
| ሎት 1 | የተለያዩ ጎማዎች | 50,000.00 | ከስቶክ |
| ሎት 2 | የማሽነሪ መለዋወጫ | 100,000.00 | በ30 ቀን |

ስለዚህ ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራና በጨረታዉ መሳተፍ የሚፈልግ አቅራቢ ድርጅት ዝርዝር የጨረታ ሰነዱን በድርጅታችን ዌብ ሳይት www.tisisat.com ማግኘት ይችላል፡፡

## የተጫራቾች መመሪያ፤

1. ተጫራቾች የዘመኑን ግብር ከፍለው የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የTIN ሰርተፊኬት፣ በዘርፉ ለመሰማራት የተሰጣቸዉን ፈቃድ እና ተያያዥነት ያላቸዉን ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
2. ጨረታው ይህ የጨረታ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15ኛው ቀን ከቀኑ 9:00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ቀን ከቀኑ 9:30 ሰዓት ባህርዳር ከተማ አባይ ማዶ ቴዲ የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ጎን በሚገኘው ዋናዉ መ/ቤት ተጫራቾች እና ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡ የጨረታው መዝጊያና መክፈቻ ቀን የስራ ቀን ካልሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተመሣሣይ ሰዓት ተዘግቶ ይከፈታል፡፡
3. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን በድርጅታችን ዌብ ሳይት www.tisisat.com ማግኘት ይችላሉ፡፡
4. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ በሰንጠረዥ የተመለከተዉን ገንዘብ በC.P.O ወይም ያለቅድመ ሁኔታ እንደተጠየቀ ለገዥ የሚከፈል (Unconditional Bank Guarantee) ማስያዝ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች በጨረታዉ ለመሳተፍ የሚያወጡት ወጪ በተጫራቹ የሚሸፈን ይሆናል፡፡
6. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያቸዉን እና ቴክኒካል ሰነዳቸዉን ለየብቻ በተለያየ ፖስታ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ተጫራች ድርጅቶች ለሚያቀርቡት ዋጋ ለእያንዳንዱን እቃ ነጠላ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋ በትክክል ሞልተው በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው፡፡

Tel:+251582204826 E-mail: contact@tisisat.com Website:www.tisisat.com
F ax: +251582204830 P.O.Box.: 840 Face Book:Tis Isat Water Works PLC

Scanned with CamScanner

7. ይህ ጨረታ በኩባንያችን የግዥ መመሪያ PR-03/2017 መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
8. ኩባንያው በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተገለፀዉ መጠን 25% ቢጨምር ወይም ቢቀንስ የጨረታ አሸናፊዉ ዉል የመያዝ ግዴታ ይኖርበታል፡፡
9. የጨረታዉ አሸናፊ አሸናፊነቱ በጽሁፍ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ 05 የስራ ቀናት ዉስጥ የጠቅላላ ዋጋዉን 10 % የዉል ማስከበሪያ ያለቅድመ ሁኔታ ለገዥ የሚከፈል (Unconditional Bank Guarantee) በማሰራት ዉል የመያዝ ግዴታ ይኖርበታል፡፡
10. የማቅረቢያ ጊዜ ከላይ በሰንጠረዡ ላይ በተገለፀዉ መሠረት መሆን አለበት፡፡ የአቅራቢዎች ዋጋ ቢያንስ ለ90 ቀናት ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ፀንቶ መቆየት አለበት፡፡
11. ኩባንያው የተሻለ አማራጭ ካገኘ በዚህ ጨረታ አይገደድም ወይም ጨረታውን በሙሉ ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
12. ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ የሚቀርብበት ቦታ ባህር ዳር ከተማ የኩባንያዉ ጽ/ቤት መሆን አለበት፡፡
13. ማሳሰቢያ፡- እንደ ኩባንያችን ፍላጎት ዉድድሩ በሎት ወይም በእያንዳንዱ እቃ ነጠላ ዋጋ መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡
14. ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥራችን 058-220-48-26 /058-320-25-48/ በፋክስ ቁጥራችን 0582204830 መጠየቅ ይችላሉ፡፡

<u>ጢስ እሳት ዉሃ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር!</u>



Scanned with CamScanner

2. ዝርዝር የተጫራቾች መመሪያ

2.1 ይህ የጨረታ ጥሪ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለተመዘገቡ አቅራቢዎችና የግብር ከፋይነት ምዝገባ ሰርቲፊኬት ላለው ሁሉ ክፍት ነው፡፡

2.2 ተጫራቾች የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ሰርተፍኬት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

2.3 ለጨረታው ዝግጅት እና ጨረታውን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ወጪ የሚችለው ተጫራች ሲሆን፣ የጨረታው ሂደት ውጤት ምንም ይሁን ምን ከዚህ በኂላ ድርጅታችን ለዚህ ዓይነት ወጪ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

2.4 ተጫራቹ በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ያሉትን መመሪያዎች፣ቅጾችና ቃሎች መመርመር አለባቸው፡፡ የሚፈለገውን መረጃ ለመስጠት ያለመቻል ወይም በበቂ ሁኔታ የተጠየቀውን የማያሟላ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ ማቅረብ በጨረታው ሰነድ ከተመለከቱት ጋር መሠረታዊ የሆነ ልዩነት ያለው ከሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

2.5 በጨረታው ለመሳተፍ ይችላል ተብሎ የሚታመን አቅራቢ በጨረታ ሰነዶች ላይ ማብራሪያ መስጠት አለበት ብሎ ሲያምን በጨረታው ሰነድ ላይ በተመለከተው ጥያቄውን ከጨረታው የማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን 3 ቀን በፊት በደብዳቤ ወይም በፋክስ መልዕክት ሊልክ ይችላል፡፡ ድርጅታችንም ከጨረታው ማቅረቢያ የመጨረሻ 3 ቀን አስቀድሞ በጨረታ ሰነድ ላይ የቀረበለት የማብራሪያ ጥያቄ ከየት እንደመነጨ ሳይጠቅስ ጥያቄው ላይ የተሰጡ ተጨማሪ ገለፃዎችን የጨረታውን ሰነድ ለገዙ ሁሉ በአድራሻቸው እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡

2.6 ድርጅታችን ከጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ ማቅረቢያ ቀን በፊት በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከጨረታው ተሣተፊ በሚቀርብለት ጥያቄ መነሻ የጨረታ ሰነዶችን ማሻሻል ይችላል፡፡

2.7 በጨረታ ሰነዶች ላይ የተደረገው ማሻሻያ የጨረታ ሰነዱን ለገዙ ተጫራቾች በደብዳቤ ወይም በፋክስ እንዲያውቁት መደረግ ያለበት ሲሆን፣ ይህም ማሻሻያ በተጫራቾች ላይ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡



Scanned with CamScanner

2.8 የጨረታ ማስከበሪያ ከሰነድ ጋር ተያይዞ ያልቀረበበት ጨረታ፣ በጨረታው የተጠየቀውን ያላሟላ ተብሎ ውድቅ ይደረጋል።

2.9 በጨረታ ሰነዶች ላይ የተደረገውን ማሻሻያ ተጫራቾች በበቂ ሁኔታ ለመመርመር ጊዜ እንዲያገኙ ድርጅታችን መወዳደሪያ ሃሳብ የማቅረቢያውን ጊዜ እንደአስፈላጊነቱ ሊያራዝም ይችላል።

2.10ተጫራቾች ጨረታቸውን ሰነድ በአማርኛ ወይም እንግሊዝኛ ቋንቋ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

3. የአሸናፊ ተጫራቾች መመሪያ

3.1 አሸናፊው ተጫራች የውል ማስከበሪያ የተ.እ.ታክስን ጨምሮ (VAT ለሚታሰብባቸዉ ግዥዎች) ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% በ CPO ወይም ያለቅድመ ሁኔታ እንደተጠየቀ የሚከፈል ባንክ ጋራንቲ ማስያዝ አለበት።

3.2 የጨረታ ማስከበሪያ ተጫራች በጨረታው አሸናፊ ከሆነ በኃላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ባይሆን ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያውን ድርጅቱ ይወርሳል።

3.4 በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ከጨረታው አሸናፊ ጋር ውል እንደተፈረመ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል።

3.5 በጨረታው አሸናፊ ለሆነው ተጫራች ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ተመላሽ የሚደረገው ውል ሲፈርም እና የውሉ ማስከበሪያ ሲያስይዝ ይሆናል።

3.6 ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ካጋጠሙ የጨረታ ማስከበሪያው ለድርጅቱ ገቢ ይሆናል።

ሀ/ ተጫራቹ በጨረታ ግምገማ ጊዜ ውስጥ ከጨረታው ራሱን ያገለለ እንደሆነ፣

ለ/ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ወይም የውል ማስከበሪያ ያላቀረበ እንደሆነ፣



Scanned with CamScanner

## 4. የጨረታ ሰነድ አዘገጃጀት እና ፊርማ

4.1 ተጫራቹ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳቡን "ዋና" እና አንድ "ቅጅ" ማቅረብ ያለበት ሲሆን በእያንዳንዱ ላይ "ዋና" ወይም "ኮፒ" የሚል ምልክት ማድረግ ይኖርበታል። በሰነዶቹ መካከል አለመጣጣም ቢፈጠር "ዋና" ተብሎ ምልክት የተደረገበት ተቀባይነት ይኖረዋል።

4.2 የተጫራቹ ሰነድ ዋና እና ቅጂዎች በታይፕ መፃፍ ወይም በእጅ ከሆነ ደግሞ በማይለቅ ቀለም መፃፍ እና በተጫራቹ ወይም በተጫራቾቹ ህጋዊ ውክልና በተሰጠው ሰው መፈረም አለባቸው። የጨረታው ሰነድ እያንዳንዱ ገጽ ፊርማና ማሕተም ሊሰፍርበት ይገባል።

## 5. የጨረታ ሰነድ አቀራረብ

5.1 ተጫራቾች በጨረታው ዋና ሰነድ እና እያንዳንዱ ቅጽ በተካተቱባቸው ፖስታዎች ላይ "ዋና" እና "ቅጅ" የሚል ምልክት በማድረግ በውስጠኛው እና የላይኛው ፖስታ ላይ ከዚህ በታች በ ተ.ቁ 1 እና ተ.ቁ 2 የተገለፁት መፃፍ አለባቸው።

1) የመ/ቤት አድራሻ

ጢስ እሳት ዉሃ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር

Tel ☎ 058-220-48-26, Fax 🖷 058-220-48-30

P.O.Box ✉ 840

ባህር ዳር

2) የጨረታውን ማስታወቂያ ቁጥር ጢእ/04/2026 በመጥቀስ ጨረታው ሚያዚያ 06/ 2018 ዓ.ም ከቀኑ 09:30 ሠዓት በፊት መከፈት የለበትም የሚል ሐረግ መፃፍ አለበት።

3) የውስጠኛውና የውጩ ፖስታ የጨረታው ሰነድ ዘግይቶ የደረሰ እንደሆነ ሳይከፈት ለተጫራቹ መመለስ እንዲቻል የተጫራቹን ስምና አድራሻ የያዘ መሆን አለበት።

4) የላይኛው ፖስታ ሳይታሸግና ምልክት ሳይደረግበት ከተላከ ድርጅታችን ለጨረታው ሰነድ መዛባረቅ ወይም ከቀኑ በፊት ስለመከፈቱ ኃላፊነት አይኖርበትም።

## 6. የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ የሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን



Scanned with CamScanner

6.1 የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ሚያዚያ 06/ 2018 ዓ.ም ከቀኑ 09:00 ሰዓት በፊት ድርጅታችን ዋናው መ/ቤት ባ/ዳር ቱዲ አሸከርካሪዎች ማሰልጠኛ ፊት ለፊት ቢሮ ቁጥር 011 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ገቢ መደረግ አለበት፡፡

6.2 ድርጅታችን በራሱ ሥልጣን የጨረታ ሰነዱ ላይ ማሻሻያ በማድረግ የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ የሚቀርብበትን የመጨረሻ ቀን ሊያራዝም ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ በሚቀርብበት የመጨረሻ ቀን ተገድቦ የነበረው የተጫራቾች እና የድርጅታችን መብትና ግዴታ እስከ ተራዘመው የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ማቅረቢያ ቀን ድረስ ይቀጥላል፡፡

7. ዘግይቶ የሚቀርብ የጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ

7.1 በድርጅታችን ከተወሰነው የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ማቅረቢያ የመጨረሻ ቀን በኋላ የደረሰ ማናቸውም የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ የተጫራቾች የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ሳይከፈት ለተጫራቹ እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

8. በጨረታ መወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ /ከጨረታ ስለመውጣት/

8.1 የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ለማቅረብ ከተወሰነው ቀን በፊት ተጫራቹ ለድርጅታችን የመወዳደሪያ ሃሳቡን የሚያሻሽል ወይም ከጨረታው ለመውጣት የሚፈልግ መሆኑን በጽሁፍ ካስታወቀ የጨረታ የመወደደሪያ ሰነድን ካቀረበ በኋላ ማሻሻያ ለማድረግ ወይም ከጨረታው ለመውጣት ይችላል፡፡

8.2 ተጫራቹ በጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ ወይም ከጨረታው ለመዉጣት የሚያቀርበው ማስታወቂያ ተዘጋጅቶ ታሽጎ እና ምልክት ተደርጎበት የሚላክ መሆን አለበት፡፡ ከጨረታው ለመውጣት የሚቀርበው ማስታወቂያ በጽሁፍ ሆኖ በደብዳቤ ወይም በፋክስ መላክ ያለበት ሲሆን የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ከሚቀርበበት የመጨረሻ ቀን በፊት የተላከ ስለመሆኑ ምልክት የተደረገበት የተፈረመ የማረጋገጫ ቅጽ በማከታተል መላክ ይኖርበታል፡፡

8.3 በጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ የመጨረሻ ቀን እና ተጫራቹ የጨረታ መወዳደሪየ ሰነድ ፀንቶ እንደሚቆይ ባመለከተው ቀን መካከለ ባለው ጊዜ ውስጠ ከጨረታ ለመውጣት አይቻልም፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ከጨረታ ውጪ ለመሆን የማያደርገው ውሣኔ ድርጅታችን የጨረታ ማስከበሪያውን ለመውረስ ምክንያት ይሆነዋል፡፡



Scanned with CamScanner

9. ጨረታን ስለመክፈት እና ስለመገምገም

9.1 ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ሚያዚያ 06/ 2018 ዓ.ም ከቀኑ 09:30 ሰዓት ድርጅታችን ዋናው መ/ቤት ባ/ዳር ቱዲ አሽከርካሪዎች ማሰልጠኛ ፊት ለፊት ቢሮ ቁጥር 011 በሚገኘው ቢሮ ይከፈታል፡፡

9.2 ጨረታው በሚከፈትበት ወቅት የተጫራቾች ስም የመጫረቻ ዋጋ እና ማሻሻያ ከጨረታ ራስን ለማግለል የቀረበ ጥያቄ እንዲሁም ተገቢው የጨረታ ማስከበሪያ የተያዘ ወይም ያልተያዘ መሆኑ እና ተጫራቹ ተገቢ ናቸው የሚላቸው ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ይገለፃሉ፡፡

9.3 በድርጅታችን በተሰየሙት የጨረታ ኮሚቴ የጨረታ አከፋፈት እና አጠቃላይ ግምገማን በተመለከተ ቃለ-ጉባኤ ይያዛል፡፡

9.4 በጨረታው መከፈቻ ወቅት ማንኛዉም የተጫራቾች ሰነድ ውድቅ አይሆንም፡፡

10. ስለጨረታው ማብራሪያ መስጠት

ጨረታውን ለመመርመር፣ለመገምገም እና ለማነፃፀር እንዲረዳ ድርጅታችን ተገቢ ነው በሚለው ጉዳይ ሁሉ ተጫራቾች ማብራሪያ እንዲሰጡ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የማብራሪያው ጥያቄ እና ለጥያቄው የሚሰጠው መልስ በጽሁፍ መሆን ያለበት ሲሆን በዋጋ ወይም በጨረታው መሠረታዊ ጉዳይ ላይ ማሻሻያ ሊጠየቅ፣ ሃሣብ ሊቀርብበት አይችልም፡፡

11. የመጀመሪያ ደረጃ ምርመራ

11.1 ድርጅታችን የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ የተሟላ መሆኑን ፣ የሂሣብ ስህተት የሌለ መሆኑን፣ የሚፈለጉት ዋስትናዎች መቅረባቸውን ሰነዶቹ በተገቢው መንገድ መፈረማቸውን እና ጨረታው በአጠቃላይ ሲታይ በአግባቡ የቀረበ መሆኑን ለመወሰን ሰነዶቹን ይመረምራል፡፡

11.2 የሂሣብ ስህተት የሚከተሉትን መሠረት በማድረግ ይታረማል፡፡

- በነጠላ ዋጋ እና በጠቅላላ ዋጋ መካከል ልዩነት ሲኖር እና ጠቅላላ ዋጋው የተገኘው ብዛት በነጠላ ዋጋ በማባዛት ሲሆን የነጠላው ዋጋ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጎ የጠቅላላው ዋጋ ይታረማል፡፡



Scanned with CamScanner

- ∇ በነጠላ ዋጋ አፃፃፍ ላይ የቦታ መለዋወጥ /Transposition/ ስህተት ቢኖረውና የተገኘው ጠቅላላ ዋጋ ትክክል ከሆነ ጠቅላላ ዋጋው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
- ∇ ተጫራቹ የተደረገው የሂሣብ ማስተካከያ የማይቀበል ከሆነ ያቀረበው የጨረታ መወዳደሪያ ሃሣብ ውድቅ ይደረጋል፡፡ ተጫራቹ ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያም በድርጅታችን ይወረሳል፡፡
- ∇ በአኃዝ እና በፊደል በተመለከተው ዋጋ መካከል ልዩነት ካለ በፊደል የተመለከተው ይወሰዳል፡፡

11.3 ወደ ዝርዝር ግምገማ ከመግባቱ በፊት ድርጅታችን እያንዳንዱ የመወዳደሪያ ሃሣብ በጨረታው ሰነድ የተጠየቀውን የሚያሟላ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ለእነዚህ ሐረጎች አፈፃፀም የተጠየቀውን የሚያሟላ የጨረታ የመወዳደሪያ ሰነድ ማለት በጨረታው ሰነድ ውስጥ ካሉት መመሪያዎችና ሁኔታዎች ጋር የሚስማማ እና መሠረታዊ ልዩነት የሌለው ነው፡፡ ድርጅታችን የጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ የተጠየቀውን የሚያሟላ መሆኑን በሚያረጋግጥበት ጊዜ መሠረት የሚያደርገው ሌላ መረጃን ሳይሆን የጨረታውን ሰነድ ይዘት ነው፡፡

11.4 በጨረታው ሰነድ የተጠየቀውን የማያሟላ የመወዳደሪያ ሃሣብ በድርጅታችን ውድቅ የሚደረግ ሲሆን፣ ተጫራቹ የነበረውን ጉድለት በማስተካከል በጨረታው ሰነድ የተጠየቀውን እንዲሟላ አድርጎ ማቅረብ አይችልም፡፡

11.5 የሌሎች ተጫራቾችን ተወዳደሪነትን የማይጎዳ እስከሆነ ድረስ በጨረታው ላይ መሠረታዊ ልዩነት የሚያስከትሉ ጥቃቅን የሥነ ሥርዓት ግድፈቶችን ወይም አነስተኛ ያለመጣጣም ሁኔታዎችን እና በጨረታው ሰነድ ውስጥ የሚታዩ መሠረታዊ ያልሆኑ ሌሎች ጉድለቶችን ድርጅታችን ሊያልፍ ይችላል፡፡

**12. ተጫራቹ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል ለመቀበል ወይም ለመሠረዝ ስላለው መብት**

12.1 ድርጅታችን እርምጃውን የወሰደበትን ምክንያት ለሚመለከተው ተጫራች ወይም ተጫራቾች የመግለጽ ግዴታ ሳይኖርበት እንዲሁም በሚመለከተው ተጫራች ወይም ተጫራቾች ላይ ለሚደረስ ጉዳት ተጠያቂነት ሳይኖርበት የጨረታው አሸናፊ ከመገለፁ በፊት በማናቸውም ጊዜ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ እና በጠቅላላ የጨረታውን ሂደት አቋርጦ ጨረታውን ውድቅ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡



Scanned with CamScanner

13. ተጫራቹ አሸናፊውን በሚመርጥበት ጊዜ የሚፈልገውን የእቃውን መጠን ለማሻሻል ስላለው መብት

13.1 ድርጅታችን አሸናፊውን በሚመርጥበት ጊዜ የውሉ ዋጋ ወይም ሌሎች የውሉ ቃሎችና ሁኔታዎችን ሳይለውጥ የእቃዎችን ብዛት ወይም መጠን እስከ 20 በመቶ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፡፡

14. አሸናፊውን ስለማስታወቅ

14.1 ጨረታው ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለቁ በፊት ድርጅታችን አሸናፊ ለሆነው ተጫራች በጽሁፍ በተዘጋጀ ደብዳቤ ወይም በማከታተል በደብዳቤ በሚረጋገጥ ፋክስ ያቀረበው ጨረታ መወዳደሪያ ሰነድ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማስታወቅ አለበት፡፡ ለተሸነፉትም በተመሳሳይ ጊዜ የተሸነፉበትን ምክንያት በማስታወቂያ ሰሌዳ ወይም በደብዳቤ ያሳውቃል፡፡

14.2 አሸናፊነትን በጽሁፍ መግለጽ ውሉ እንደተመሰረተ አያስቆጠርም፡፡ ውል ተመስርቷል የሚባለው ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች እቃዎችን ለመሸጥና ለመግዛት ስምምነታቸውን በጹሁፍ በማስፈር ከተፈረሙበት ነው፡፡

14.3 አሸናፊው ተጫራች ውሉን በመፈረም ከውል ማስከበሪያ ጋር ሲያቀርብ ድርጅታችን በጨረታው ለተሸነፉት ሁሉ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

15. ውሉ ስለመፈረም

15.1 ድርጅታችን ተጫራቹ ያቀረበው የመወዳደሪያ ሰነድ የተመረጠ መሆኑን በሚገልጽበት ጊዜ ከጨረታው ሰነድ ጋር የቀረበውን በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል የተገቡትን ስምምነት በሙሉ ያካተተ በጨረታ ሰነድ ከተገለፀው መሰረታዊ የውል ይዘት በተጨማሪ ዝርዝር ውል አብሮ ይልካል፡፡

15.2 አሸናፊ ተጫራች የውሉ ሃሳብ በደረሰው በ 05 ቀናት ጊዜ ወስጥ ፈርሞ እና ቀኑን ሞልቶ ከውል ማስከበሪያ ጋር ለድርጅታችን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

Tel:+251582204826 E-mail: contact@tisisat.com Website:www.tisisat.com
F ax: +251582204830 P.O.Box.: 840 Face Book:Tis Isat Water Works PLC

Scanned with CamScanner

## ሎት 1: የተለያዩ ጎማዎች

| ተ/ቁ | የዕቃዉ አይነት | መለኪያ | ብዛት | ነጠላ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | Remarks |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | Tyre 12.00R20 with inner tube.<br>Rear (30)<br>Play rate = 22PR<br>Load index to speed ratio (158/155F)<br>Type = TT | PCS | 30 | | | |

ማሳሰቢያ፤

- ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸዉ ጎማዎች ቴክኒካል ሰነድ ማያያዝ አለባቸዉ።
- ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸዉ ጎማዎች የጎማዎችን የስራት ሀገር (ORIGIN) እና የጎማዉን አይነት (BRAND) መግለፅ አለባቸዉ።
- ተጫራቾች የሚወዳደሩባቸዉ ጎማዎች ወደ ዉስጥ የተቀረፀ መለያ ቁጥር (SERIAL NUMBER) ሊኖራቸዉ ይገባል።

Tel:+251582204826 E-mail: contact@tisisat.com Website:www.tisisat.com
F ax: +251582204830 P.O.Box.: 840 Face Book:Tis Isat Water Works PLC

Scanned with CamScanner

Tis Isat water works plc
ጢስ እሳት ውሃ ስራዎች ኃ/የተ/የግል/ማ

## ሎት 2: የማሽነሪ መለዋወጫ

| No | Description | Part No | Unit | Qty | Unit price with vat | Total price with vat | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01 | Foam pump assay /Water injection system specification<br>□ Type Caterpillar (CAT)<br>□ Capacity 0-45.4L/min(0-12gal/min)<br>□ pressure 550psi (37.9bar) (3,792kpa) | Foam pump part no = 2652154473 Hydraulic Motor part no = 2670514153 | Assay | 02 | | | Foam pump part no = 2652154473<br>Hydraulic Motor part no =2670514153<br>Model= 2525.3000 (Cat pumps) |
| 02 | Foam pump for massenza rig | PSP93 | Pcs | 01 | | | For massenza rig (MI 28) |
| 03 | Hand pump fpt iveco cruiser 9 | | Pcs | 03 | | | |
| 04 | Regulating valve assay original sealed | 1604707982 | Pcs | 04 | | | |
| 05 | Air hose 3" Bale 2 shibo, Standard = EN 857 2SC extension, Nominal diameter (dn) = 76, Dash size = - 48<br>Internal diameter 3"<br>Working pressure 45 bar or 650 psi genuine. | | Mtr | 08 | | | Manuli tractor /2k |
| 06 | Wiper blade with arm and motor assay complete | | Assay | 01 | | | For Daewoo crane<br>Model = K7C6F, |
| 07 | Engine stop switch | | Pcs | 04 | | | |



Scanned with CamScanner

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 08 | **Connecting rod** | | Set | 04 | | | 750L Mixer (Lombardini mixer, Model = 25LD425/2B1) |
| 09 | **Piston** | | Set | 04 | | | |
| 10 | **Piston ring** | | Set | 04 | | | |
| 11 | **Cylinder liner** | | Pcs | 04 | | | |
| 12 | **Intake and exhaust valve** | | Set | 02 | | | |
| 13 | **Cylinder head gasket** | | Set | 02 | | | |
| 14 | **Gear box pulley** | | Pcs | 02 | | | |
| 15 | **Gear box complete /assay/** | | Pcs | 02 | | | |
| 16 | **Piston ring** | | Pcs | 02 | | | For mossa generator Model= TS 200 DES-CF |
| 17 | **Piston with pin** | | Pcs | 02 | | | |
| 18 | **Connecting rod with shell bearing** | | Pcs | 02 | | | |

1. የድርጅቱ ስም፡ ............................................

ቀን ............................

ፊርማ ...........................

Tel:+251582204826 E-mail: contact@tisisat.com Website:www.tisisat.com
F ax: +251582204830 P.O.Box.: 840 Face Book:Tis Isat Water Works PLC

Scanned with CamScanner